# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 117 ነሃሴ 6 ቀን 2002 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**"የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:"**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው**

## ዘረኛውና የወያኔ አገዛዝ ለስለላ ያሰለጠናቸውን የትግራይ ብሔር አባላት በተለያዩ የአገሪቱ ወረዳዎች በአማካሪነት እየመደበ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ከትግራይ ብሔረሰብ ተመልምለው ከአንድ አመት በላይ የስለላ ሙያ ስልጠና ሲሰጣቸው የቆዩ ወጣቶችን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ወረዳዎች በአማካሪነት ስም እየመደበ መሆኑን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከሰሜን ኢትዮጵያ ባስተላለፈው ዘገባ አስታውቋል።

ወያኔ ከግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት በኋላ ባካሄደው ግምገማ፣ ታማኝነታቸው በጥርጣሬ ላይ የወደቀውን ጨምሮ በርካታ ካድሬዎቹን ማባረሩ ይታወሳል። በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የተቃውሞ መንፈስ በመረዳቱ በራስ ያለመተማመን የሚያጠቃው አገዛዝ የሌላ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ ሎሌዎቹን የማያምንበት ደረጃ ላይ ደርሷል። የስልጣን ቁጥጥሩን ለማጥበቅም፣ የአገሪቱን ወረዳዎች ከዘር ትስስር የተነሳ ፍጹም ታማኞቼ ይሆናሉ በሚላቸው ሰላዮች ለማስጠበቅ ተነስቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የከፍተኛ ትምህርት እድል ከተሰጣቸው የሰሞኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጠና ሰለባዎች ውስጥ ከ 80 በመቶ በላይ የሚሆኑት የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያውያን በሙሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን እንዲቀበሉ ለማድረግ ባለው እቅድ ሰሞኑን መቀሌና አዳማ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በግዴታ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስልጠና እንዲወስዱ የተደረጉት የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሰቃዮች ስልጠናቸውን አጠናቀዋል። ስልጠናውን ከተከታተሉት ውስጥ 200 የሚሆኑት የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት እንዲከታተሉ እድሉ የተሰጣቸው ሲሆን የትምህርት እድሉን ካገኙት ውስጥም ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከትግራይ ክልል ውስጥ መሆኑን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከናዝሬት በላከልን ዘገባው ላይ ገልጿል።

ዘጋቢያችን ያናገራቸውና ስማቸውም እንዳይገለጽ ያስጠነቀቁ የስልጠናው ተሳታፊዎች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልጠናው የተሳተፍን ተማሪዎች ከበርካታ ክልሎች ሆነን እያለ ለምን 80 በመቶ የሆነው የከፍተኛ ትምህርት እድል ለትግራይ ክልል ተወላጆች ብቻ እንደተሰጠና ለዚህም መስፈርቱ ምን እንደሆነ አናውቅም በማለት ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ምሩቃን በውጤታቸው ምክንያት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲያስተምሩ የታጩ መሆናቸውንና፤ ከመጪው ሙያቸው ጋር የተያያዘ ስልጠናን በመስጠት ስም በአዳማ እና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲዎች ተሰብስበው ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲሰበኩ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

## ወያኔ በኦሮሚያ እና በደቡብ የገጠር ቀበሌዎች በስራ ላይ ያዋላቸውን የቁጥጥር መዋቅሮች ወደ ሌሎች ክልሎች ሊያስፋፋ ነው ተባለ

የወያኔ አገዛዝ ባለፉት በርካታ አመታት በአንዳንድ የኦሮሚያ እና የደቡብ ክልሎች አካባቢዎች በስራ ላይ ያዋላቸውን ከቀበሌ ያነሱ የቁጥጥር መዋቅሮች ወደ አፋር፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ክልሎች ለማስፋፋት በዝግጅት ላይ መሆኑ ታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከኢትዮጵያ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ መሰረት፥ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ የሚመራ ቡድን በነዚህ ክልሎች "የገበሬ መንደር" የሚባል መዋቅር መመስረት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ጥናት ለማካሄድ ተቋቁሞ ከሁለት ወራት በፊት ስራ መጀመሩን ለሂደቱ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዘጋቢያችን ገልጸዋል። አራቱ ክልሎች ለረዥም ጊዜ ወያኔን በትጥቅ የሚታገሉ ሃይሎች የሚንቀሳቀሱባቸው እንደሆኑ ይታወቃል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለዚህ ጉዳይ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት መቶ በመቶ ማሸነፉን ያወጀው ወያኔ፣ ስለምርጫው ትክክለኛነት ህዝቡን ለማሳመን ዘመቻ መጀመሩ ታውቋል

የወያኔ አገዛዝ በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት መቶ በመቶ መርጦኛል ያለውን ህዝብ መልሶ ስለምርጫው ትክክለኛነት ለማሳመን ዘመቻ መጀመሩን የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ዘገባ አስረድቷል።

በወያኔ ቁጥጥር ስር በሚገኙ የህዝብ መገናኛ ብዙሃን ተቀጥረው የሚሰሩ ልማታዊ ጋዜጠኛ ተብዬዎች በተለያዩ ክልሎች የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ወያኔ የፓርላማውን መቀመጫ ሙሉ በሙሉ ማሸነፉ በስራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደማያስከትል ህዝቡን ለማሳመን በመጣር ላይ መሆናቸውን ዘገባው ገልጿል።

የውይይት መድረኮቹ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ያሳተፉ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን፤ ምርጫው ፍትሃዊ እንደሆነና ህዝቡ ወያኔን የመረጠውም ገዢው ፓርቲ ከነሱ የተሻለ ስራ መስራቱን አስተውሎ ነው በማለት ሲናገሩም ተደምጠዋል። አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ግለሰቦች ወይ ማስፈራሪያ ተደርጎባቸው፤ አልያም በሆድ አደርነት የሚሳተፉ ናቸው ብለው እንደሚጠረጥሩ ለዘጋቢያችን ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በወልቃይት ጠገዴ እና በተቀረው የአገሪቱ ክፍል የሚደርሰውን ግፍ ለማስቆም የትብብር ትግል ጥሪ ተደረገ

በወልቃይት ጠገዴ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን ግፍ ለማስቆም የኢትዮጵያውያን የትብብር ትግል አስፈላጊ ነው ሲሉ ልሳነ-ግፉአን የተባለ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ምክትል ሊቀመንበር ገልጸዋል።

አቶ አባይ መንግስቱ ለግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ፥ ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ወልቃይት ጠገዴን ከተቆጣጠረ ወዲህ በአካባቢው ነባር ነዋሪ ላይ ሲፈጽም የቆያቸውንና በጆሮ ለመስማት የሚሰቀጥጡ ግፎች ዘርዝረዋል። የወያኔ አገዛዝ ወልቃይት ጠገዴን በሰባዎቹ መጨረሻ ላይ ተቆጣጥሮ፤ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ አካባቢውን ከጎንደር በመንጠቅ ወደ ትግራይ ክልል መጨመሩ ይታወቃል።

በወቅቱ ሁኔታውን የተቃወሙ የአካባቢው ነዋሪዎች እና ታሪካቸውን የሚያውቁ በሺዎች የሚቆጠሩ አዛውንቶች የት እንደደረሱ እንደማይታወቅ፤ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎችም ለእስር እና ለግድያ፤ እንዲሁም እርሻቸው እየተነጠቀ ለስደት እንደተዳረጉ አቶ አባይ አስረድተዋል። በአንፃሩ ግን በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ከትግራይ መጥተው እንዲሰፍሩ እና የእርሻ መሬት እንዲሰጣቸው እንደተደረገ ተናግረዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ቃል ገብቶ ያልፈጸመው የወያኔ አገዛዝ አሁንም የምግብ ዋስትናን አረጋግጣለሁ ሲል ደሰኮረ

የወያኔው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ሱፊያን አህመድ፥ "ኢትዮጵያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በአለም ፊት በተመጽዋችነት ስሟ አይነሳም" ማለቱ የወያኔው አገዛዝ ከዚህ ቀደም የገባቸውን ተመሳሳይ ቃላት እንዳስታወሳቸው የፖለቲካ ተንታኞች ገልጸዋል።

የቀድሞው የወያኔ ታጋይ አማረ አረጋዊ ንብረት የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ እንደዘገበው፣ ሱፊያን አህመድ ይህንን የተናገረው የአገዛዙን የመጪ አምስት አመታት እቅድ በሚመለከት በሰጠው መግለጫ ነው። ሱፊያን፥ አገዛዙ ከያዛቸው እቅዶች ውስጥ አንዱ የአገሪቱን የእህል ምርት ከእጥፍ በላይ በማሳደግ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው ብሏል። ሱፊያን በዚህ የእቅድ ዘመን ማብቂያ ላይ የምግብ እጥረት እንደማይኖር፤ ቢኖር እንኳ አገዛዙ የራሱን ገንዘብ ተጠቅሞ እህል እንደሚገዛ እንጂ እርዳታ ፍለጋ እንደማይሄድ አስረግጦ ተናግሯል።

ጉዳዩን በሚመለከት ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡ የፖለቲካ ተንታኝ፥ የሱፊያን ንግግር አገዛዙ ከዚህ ቀደም ከተናገራቸው ምንም እንደማይለይ ገልጸው፤ በተለይም መለስ ዜናዊ የዛሬ ሃያ አመት ግድም ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአምስት አመታት ውስጥ በቀን ሶስት ጊዜ መመገብ የሚችሉበት ደረጃ እንደሚያደርሳቸው መደስኮሩ ፈጽሞ እንደማይረሳ አስታውሰዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ሁለገብ ትግሉ ዲያስፖራው ደጃፍ መጥቶለታል፤ ለእራሳችንና ለአገራችን ነፃነት በአርበኝነት እንነሳ!

የወያኔ ዘረኝነት፣ ትምክህት እና የስሌት ስህተት እርስበርስ የሚመጋገቡ ናቸው። ትዕቢቱ "ስህተቱን" ግዙፍ ሲያደርገው፤ ዘረኝነቱ ደግሞ "ስህተቱን" አስነዋሪና አሳፋሪ ያደርገዋል። በዘረኝነትና ትዕቢት ከተነዱ በርካታ ስህተቶች አንዳንዱን ለአብነት ያህል እናንሳ።

1. ወያኔ ለእኩልነት ታገልኩ ብሎ ለዘረኝነት ተቋማዊ መሠረት ሰጠ። ማንም እንደሚገነዘበው ለእኩልነት በመታገል እና ዘረኝነት በማስፈን መካከል ያለውን ልዩነት የትየለሌ ነው። ይህም በመሆኑ "እኩልነትን አሰፈንኩ" ባለበት አገር ለእኩልነት የሚታገዙ ቡድኖች ተበራከቱ። በአፉ እኩልነትን እየሰበከ በተግባር ግን ለአፓርታይድ ሥርዓቱ "የህግ ጥበቃ" አኖረለት፤

1በዚህ አጋጣሚ ታቦ ኢምቤኪ የአገራቸውን አፓርታይድ ሥርዓት ተዋግተው አሸንፈው እና አዲስቷን አገራቸው መርተው ለተረኛ ከለቀቁ በኋላ አሁን በአፓርታይድ ሥርዓት ለምትገኘው ኢትዮጵያ ዜጎች አዲስ አበባ ውስጥ ያደረጉትን ጥሪ ልብ ማለት ተገቢ መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን።

2. የኢትዮጵያን ሕዝብ "በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ አደርጋለሁ ብሎ" ብሎ መዋሸቱ ሳያንስ የራሱን በልተው የማይጠግቡ ሆዳሞችን ተመልካቾች እንድንሆን አድርጎናል። ከዚህም አልፎ የራሱ ሰዎች መጥገብ፤ የእሱ ሰዎች መንፈላሰስ የአገሪቷ ልማት ማስረጃ አድርጎ በማቅረብ ይሳለቅብናል፤
3. "ከእንግዲህ የጥይት ድምፅ አይሰማም" ባለን ማግሥት በአስርት ዓመታት ጦርነት ካለቀው ሕዝብ ብዛት ጋር የሚስተካከል ብዛት ያለው ወጣት ምክንያቱም፣ ውጤቱም ባልታወቀ ጦርነት አስጨረሰ፤
4. በ1997 ዓም "ሕዝብ ይወደኛል" ብሎ በማሰቡ፤ እግረ መንገዱን ለእርጥባን እንዲረዳው በትንሹ ከፈት ያለ ምርጫ ቢሞክር ከገጠር እስከ ከተማ ተዋረደ። በዚህም መነሻነት ህፃናት፣ ወጣቶችና አዛውንት በአደባባይ ታረዱ። አገራችን በአግዓዚ ጦር ታመሰች፤
5. ሶማሊያን ሌላ የእርጥባን ምንጭ ለማድረግ ሲል "ሞቃዲሾ ውስጥ የሰደቡኝን ሰዎች በወር ውስጥ ደምስሻቸው እመጣለሁ" ብሎ ገብቶ ከፊሎቹን አንግሶ፣ ከፊሎቹን ደግሞ አጎልብቶ፤ በሶማሊያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ቂምን ተክሎ በመመለሱ እኛ ከእኛ አልፎ ለሌሎችም የተረፈ መዘዝ አስከትሎብናል፤
6. አባላትን ለማብዛት ብሎ ምልመላ ቢያጧጡፍ የወያኔ አባል መሆን በቀበሌ ነዋሪነት የመመዝገብ ያህል እንኳን ትርጉም ያለው ነገር ሊሆን አልቻለም፤
7. የ97 ቱን ቁስል በ2002 እሽራለሁ ብሎ ካድሬዎቹን ቢያሰማራ ከአዘራረፍ ቁጥብነት ማጣት "መቶ በመቶ አሸንፈሃል" የሚል መርዶ መጣበት።

የወያኔ በዘረኝነትና ትዕቢት የታጀቡ የስሌት ስህተቶችን ዘርዝሮ መጨረስ ያዳግታል፤ እንዲያዉም ከስህተቱ ተምሮ ሊሻሻል የማይችል መሆኑን በየእለቱ እያረጋገጠልን ነው።

ወያኔ አሁንም ለከፋ ስህተት ታጥቆ ተነስቷል። በተሳሳቱ ስሌቶች በነፈዘ ጭንቅላቱ ዛሬ ኢትዮጵያ በቁጥጥሩ ሥር ነች። ወያኔ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ገብሯል" ብሎ ራሱን አሳምኖ ጨርሷል። የቀረው ዲያስፖራ ነው። እናም ዲያስፖራን ሊያስገብር እቅዱን ነድፎ ፈታውራሪዎቹን አዝምቷል።

ወያኔ ወደ ዲያስፖራ ሲዘምት ከሶማሊያው ዘመቻ ባላነሰ የገዛ ራሱን ማጥ ውስጥ እየጨመረ እንደሆነ አልታወቀውም። ዲያስፖራን ሊያንቅ ባዘጋጀው ገመድ ራሱ ሊታነቅበት እንደሚችል አልታየውም። እናም የእውር ድንብሩን እየፎከረ ነው።

ወያኔ የዲያስፖራ ዘመቻውን "አገራዊ" ቀለም ለመቀባት ቢሞክርም የሚታለል እንደሌለ አይገባውም። አባይ ወንዝ እና "ልማት" የተሰኘውም ቃል ለማጭበርበሪያነት መዋል የጀመሩት ዛሬ አይደለም። ወያኔ በቤተ-ክህነት በኩል አንጓት ማስገባት የጀመረውም አሁን አይደለም። የሚጠቀማቸው ስልቶች ች በሙሉ ያረጁና ዋጋ የሌላቸው ናቸው።

የወያኔ መሠረቱ ዘረኝነት ነው። ይህ ለኢትዮጵያዊን ግልጽ ከሆነ ቆይቷል። የፈለገውን ቀለም ቢቀባባው ሊደበቅ አይችልም። የወያኔ ተግባራት የሚያጠነጥኑት ይኸው ዘረኛ የሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ ፓሊሲ በማስፈፀም ላይ መሆኑ አሁን ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግልጽ ሆኖለታል ብለን እናምናለን።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነው በላይ ወያኔ በዲያስፖራ ውስጥ ተለይቶና ተነጥሎ የተቀመጠ ነው። ሰላዮቹ ይታወቃሉ። ሌላው ቀርቶ ለዚህ ዘመቻው በስደተኝነት ስም የገቡት ዝርዝራቸው ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ለኢትዮጵያዊያን ያዘጋጀውን መርዝ ራሱ እንዲጨልጠው ማድረግ ቀላል ነው።

ከኢትዮጵያ ውጭ ላለ ኢትዮጵያዊ ጠላት እበራፉ ድረስ የመጣለት በመሆኑ ብዙ ጣጣ ቀንሶለታል። በዚህም ምክንያት በዲያስፖራ ለሚገኙ ወገኖቻችን የምናስተላልፈው መልዕክት ይህ ነው - አሁን ፍልሚያው እደጃችሁ ነው!!!

የወያኔ ወደ ዲያስፖራ መዝለቅ የአገርቤቱን እና የውጭውን ትግል ለማቀናጀት አዲስ አጋጣሚ ፈጥሮልናል፤ እንጠቀምበት። አሁን "ውጭ"፣ "ውስጥ" ማለት ቀርቷል። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይንቃ! በየመድረኩ፣ በመንደሩ ወያኔን ያዋርድ! ይህ ነው ሁለገብ ትግል ማለት!!! ሁሉም ለራሱና ለኢትዮጵያ ነፃነት ይቁም!!! ሁላችንም በአርበኝነት እንሰለፍ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

### ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለስለላ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህም አኳኋን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከትግራይ እና ከሌሎች ክልሎች የተመለመሉ ትግራውያን ወጣቶችን በስለላ ሙያ ሲያሰለጥን መቆየቱ ታውቋል። ሰላዮቹን በአገሪቱ ዙሪያ ባሉ ወረዳዎች የሚመድበውም ይኸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሲሆን፤ ተጠሪነታቸውም ለሚኒስትሩ ዶ/ር ሽፈራው ተክለማርያም መሆኑን ዘገባው አስረድቷል። ሰላዮቹ በአማካሪነት ስም ይመደቡባቸው እንጂ የወረዳ አስተዳደሮቹም ሆኑ የየክልሎቹ መንግስታት ሊያዙና ሊቆጣጠሯቸው እንደማይችሉ ለማወቅ ተችሏል።

እነዚህ የወያኔ ዘረኛ ስርአት ጠባቂዎች ለሚሰሩት ስራ ከበቂ በላይ የሆነ ወርሃዊ ደሞዝ ሊሰጣቸው የታቀደ ቢሆንም፤ ተጨማሪ የቀን አበል እንዲጨመርላቸው እና ይህም እየተጠራቀመ በአመት ሁለት ጊዜ እንዲከፈላቸው በጀት ተመድቦላቸዋል። መረጃውን ለዘጋቢያችን ያቀበሉት ምንጮች፥ ይህ ወያኔ አገሪቱን እየዘረፈ የአንድ ብሔር ተወላጆችን የሚጠቀምበት አንድ ተጨማሪ መንገድ መሆኑ ነው ብለዋል። ጉዳዩን በሚመለከት አስተያየት የሰጡን የፖለቲካ ተንታኝ ደግሞ፥ ሁኔታው በደቡብ አፍሪካ የነበረው የአፓርታይድ አገዛዝ ነጮችን ለመጥቀም ሲል አዳዲስ እና አላስፈላጊ ስራ ይፈጥር የነበረበትን ሁኔታ እንዳስታወሳቸው ገልጸውልናል።

### በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት መቶ በመቶ ማሸነፉን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡ የፖለቲካ ተንታኝ፥ "ወያኔ 'ህዝቡ ሙሉ በሙሉ ድምጽ ሰጥቶኛል፤ ከዛም በኋላ በየከተማው ሰልፍ እየወጣ በማሸነፌ ደስታውን ገልጿል' እያለ ሲፎክር ሰንብቶ፤ መልሶ ምርጫው ትክክለኛ እንደሆነ ህዝቡን ለማሳመን ዘመቻ መጀመሩ እርስ በርሱ የሚጣረስ እና የአገዛዙን በራስ ያለመተማመን የሚያሳይ ነው" ብለዋል።

### ወያኔ በኦሮሚያ እና በደቡብ የገጠር ቀበሌዎች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ልዩ ትኩረት ሰጥቶት እየሰራ ያለ ሲሆን፤ ከአዲሱ ለገሰ በተጨማሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የትግራይ እና የደቡብ ክልል ፕሬዚደንቶች የቡድኑ አባላት እንዲሆኑ መደረጉ ታውቋል። የመንደር ምስረታው እቅድ እና አፈፃጸም የሚካሄደው የስራው ባለቤቶች ከሆኑት ክልሎች ውጭ በሆኑ የሌሎች ክልሎች ፕሬዚደንቶች እና ካድሬዎች መሆኑም ለጉዳዩ ቅርበት ባላቸው ሰዎች ዘንድ አነጋጋሪ ሆኖ መቆየቱን የደረሰን ዘገባ አስረድቷል። የአፋር ክልል ጉዳይ በትግራይ ክልል ፕሬዚደንት፤ የሶማሌ ክልል በኦሮምያ ፕሬዚደንት፤ የጋምቤላ ክልል በደቡብ ፕሬዚደንት፤ እንዲሁም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአማራ ፕሬዚደንት ክትትል እና ቁጥጥር ስር መደረጉ ታውቋል። ይህ ስራው በሚካሄድባቸው ክልሎች ሰዎች ላይ እምነት ከማጣት የመነጨ ይሁን ለሌላ ምክንያት ግልጽ እንዳልሆነ ዘጋቢያችን ገልጿል።

### ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ቃል ገብቶ ያልፈጸመው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛው አምባገነን ለሃያ አመታት በስልጣን ላይ ከቆየ በኋላ ወደ አስራ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ የእርዳታ ጥገኞች እንደሆኑ እና በቅርቡ በአክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እና የተባበሩት መንግስታት ትብብር የወጣ ሪፖርት እንደሚያሳየው ደግሞ፤ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ህዝብ በድህነት ውስጥ እንደሚማቅቅ ይታወቃል።

ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየት የሰጡት ሌላኛው የፖለቲካ ተንታኝ ደግሞ "የአገዛዙ ብቸኛ አላማ ለሚሞኙለት ኢትዮጵያውያን የሃሰት ተስፋን መስጠት እና ይህንን እቅድ ተብዬ አስታኮ ከአለማቀፉ ማህበረሰብ ተጨማሪ እርዳታ በመሰብሰብ የገዢውን ፓርቲ ኩባንያዎች እና ባለስልጣናት ማበልጸግ ነው" ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## የደቡብ አፍሪካ ፕሬዜዳንት ታቦ ኢምቤኪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመርቂ ተማሪዎች በዓል ላይ በመገኘት የተደረገላቸውን የክብር የዶክትሬት ማዕረግ ሲቀበሉ ያደረጉት ንግግር ሐምሌ 17 2002 (JULY 24, 2010)

ክቡራትና ክቡራን፡-

ፕሬዚደንት እንድሪያስ እሸቴን እና ዩኒቨርቲሲውን ባጠቃላይ ይህንን አንጋፋ አፍሪካዊ የትምህርት ማእከል እንደ ክቡር ተመራቂ እንድቀላቀል ስለሰጡኝ ክብር እና ልዩ ስጦታ ከልቤ ላመሰግን እወዳለሁ። ይህ ከኢትዮጵያ ጋር ልዩ ትስስር የሚሰጠኝ አዲስ ሁኔታ፣ በብዙ መንገድ ወደ እናት አገር ከመመለስ ጋር የሚተካከል ነው።

ዘመናዊው የአፍሪካ የነፃነት ንቅናቄ የመነጨው ወደ 19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ በደቡብ አፍሪካ ነው ብል ትክክል ይመስለኛል። ይህ ንቅናቄ ከመጀመሪያው ጀምሮ ይገፋ የነበረው በሁለት አላማዎች ነበር፡-አንደኛው የሁሉም አፍሪካውያን ነፃነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በአፍሪካ-ገብ/ፓን-አፍሪካ አጀንዳ እና አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ የአፍሪካ መሻሻል ነበር።

የዚህ ቅናቄ የቀድሞ መስራቾች የአገራችን የመጀመሪያዎቹ ዘመናዊ አፍሪካውያን ልሂቃን ናቸው። የተነሱትም ከቤተክርስቲያናት ትምህርት ቤቶች ሲሆን፤ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን የቤተክርስቲያን አገልጋዮችም ነበሩ።

እነዚህ ዘመናዊ የአፍሪካ ልሂቃን ከአውሮፓውያን ሚሲዮኖች እራሳቸውን አላቀው በቤተክርስቲያናቱ ላይ ባለቤትነታቸውን ሲያውጁ፣ እንደመነሳሻ የተጠቀሙት የመጽሃፍ ቅዱስ ቃል በመዝሙረ ዳዊት ምእራፍ 68 ላይ ይገኛል። ይህም፥ "መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለው ነው።

እንደ ቅኝ ተገዢዎች፣ አፍሪካ የአውሮፓውያን የቅኝ ግዛት እሽቅድድም ሰለባ ሆና በነበረችበት ወቅት ኢትዮጵያ ነፃነትዋን እንደያዘች መቀጠሏ መነሳሳትን ይሰጣቸውን ነበር። እናም በመጽሃፍ ቅዱስ እንደተተነበየው ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ስትዘረጋ ቤተክርስቲያናታችንን በአፍሪካዊ ስነ-ምግባር ትሞላለች ብለው ያምኑ ነበር።

ይህች እውነተኛ የአፍሪካ ቤተክርስቲያን ደግሞ አፍሪካውያን በሙሉ ለነፃነት፤ እንዲሁም ባህላቸው፣ ማንነታቸው እና ሰብአዊነታቸው እንዲከበር ላላቸው ህልም እንደ ማከማቻ ቦታ ሆና ታገለግላለች ብለው ያምኑ ነበር።

ታዲያ ባጋጣሚ አይደለም እነዚህ የጠቀስኳቸው ቤተክርስቲያናት እራሳቸውን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ብለው የሰየሙት።

በአህጉራችን ላይ የመጀመሪያው ዘመናዊ ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄ የሆነው የደቡብ አፍሪካው "አፍሪካን ናሺናል ኮንግረስ" የተወለደውም ከነዚሁ ከአገራችን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ነው። ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄያችንን ይነዳ የነበረው የአፍሪካዊነት ብሔራዊ ስሜትም የሚገለጸው ኢትዮጵያዊነት በሚለው ስም ነበር። እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1906፣ የአፍሪካ ናሺናል ኮንግረስ እናት የነበረውና "የሳውዝ አፍሪካ ኔቲቭ ኮንግረስ" የተባለው ድርጅት ይህን ብሎ ነበር፡-

> "ኮንግረሱ ኢትዮጵያዊነት በአፍሪካውያን እና በአውሮፓ ስልጣኔ መነካካት የተፈጠረ የተራማጅነት ምልክት ነው ብሎ ያምናል። ይህም በማህበራዊ፣ በሃይማኖት እና ምጣኔ ሃብት ዘርፎች ሁሉ እራሱን ይገልጣል።"

በዛው አመት፥ የደቡብ አፍሪካው ቅኝ አገዛዝ ገዢ የአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ የመጀመሪያ ፕሬዚደንት የሆኑትን ቄስ ጆን ዱቤን በሚመለከት፥ "ይህ ሰው የታወቀ ኢትዮጵያዊ ነውና ክትትል ሊደረግበት ይገባል" ብሎ ነበር።

ታዲያ ዛሬ የእኔ እዚህ መገኘት ወደ እናት አገር እንደመመለስ ነው ስል አሁን ይገባችኋል። ወደ እናት አገር ተመልሻለሁ የምልበት ምክንያት ኢትዮጵያ ከዛሬ መቶ አመት በፊት እና ከዛም ባሻገር ያደረገችው ነው። የነፃነት ንቅናቄያችን እንዲወለድ ከማነሳሳቷ በተጨማሪ፣ በአህጉራችን ላይ ኩሩ እና ነፃ አገር ሆና መቆየቷ ኢምፔሪያሊዝምን እና ቅኝ አገዛዝን ድል እንደምንነሳ ያሳወቀን ጠንካራ ማረጋገጫ ነበር።

በዚህም አኳኋን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ልዩ የሆነ ቦታ በመያዝ፣ ለአፍሪካውያን በሙሉ እንደ ማእከላዊ የመሰባሰቢያ ሃሳብ ሆና አገልግላለች። እራሷ እንደ ምሳሌ በመሆን አፍሪካውያን አንድ እጣ ፈንታ እንዳላቸው በመረዳት በመተባበር ለነፃነታቸው እንዲታገሉ አነሳስታለች።

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1896 የተፈጸመው የአድዋ ድል ለአፍሪካ እና ለተቀረው አለም ምን አይነት ትርጉም እንዳለው ትረዳላችሁ። ድሉ ከተፈጸመ ከአጭር ጊዜ በኋላ አንድ ፈረንሳዊ የታሪክ ጸሃፊ አውሮፓውያንን እንዲህ ብሏቸው ነበር፡-

> "የጣሊያኖች በንጉስ ሚኒሊክ መሸነፍ...አፍሪካዉያን እስካሁን ድረስ በንቀት አረመኔዎች ናቸው እያሉ ሲገዟቸው በቆዩት አውሮፓዉያን ላይ እንዲነሱ የሚያነቃቸው ነው። አንድ መረሳት የማይገባው ነገር፥ አሁን ወደ አረመኔነት ተቀይረዋል ከምንላቸው አገራት ውስጥ በብዙዎቹ ውስጥ እጅጉን የመጠቀ ስልጣኔ እንደነበር ነው። በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያ ከስልጣኔዋ እና ከሃብቷ የተነሳ በአፍሪካ ሁሉ ውስጥ ታላቅ ታዋቂነትን አትርፋ ነበር። የሚኒሊክ ድል የአፍሪካ ሁሉ ድል ነው። በነዚህ ሃገራት ውስጥ አፍሪካ አውሮፓን እንደተቆጣጠረች መሰማት ጀምሯል፤ ነገም ይቀጥላል። በጣሊያኖቹ ሽንፈት ልንደሰት አይገባም። ያ ሽንፈት የኛም ሽንፈት ነው፤ የቅኝ ገዢዋ እና የነገዋ አውሮፓ ሽንፈት ነው።"

ከብዙ አመታት በኋላም የአድዋ ድል ለአፍሪካውያን ሁሉ የኩራት ምንጭ መሆኑን ቀጠለ። አፍሪካ ልዩ እና አስፈላጊ የሆነን አስተዋጾ ለሰው ልጆች ስልጣኔ ማበርከት እንደምትችልም በራስ መተማመንን ሰጠ።

ይህንን በሚመለከት፣ በአድዋ ድል በአስረኛ አመት የአፍሪካ ናሺናል ኮንግረስ መስራች የሆኑት አቶ ፒክስሊ ሰሜ ሲጽፉ፡- "ይህ የአፍሪካ መነቃቃት አዲስ እና ልዩ የሆነ ስልጣኔ በቅርቡ ወደ አለም እንደሚጨመር ጠቋሚ ነው። የዚህ አዲስ ስልጣኔ ዋና ገጽታ ደግሞ መንፈሳዊነት እና ሰብአዊነት ናቸው፤ በርግጥም ሞራላዊ እና ዘላለማዊ የሆነ መነቃቃት ነው!" ብለው ነበር።

የዘመናችንን ችግሮች ለመወጣት እና ሰሜ በአድዋ ድል በአስረኛው አመት እንዳሉት አዲስን ስልጣኔ ወደ አለም ለማምጣት በአንድነት ለመነሳት የሚያስችለን፤ ያኔ ኢትዮጵያ ያበረከተችውን አይነት ማእከላዊ የመሰባሰቢያ ሃሳብ በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አለን ወይ ብለን እዚህ የተሰበሰብነው እራሳችንን ለመጠየቅ ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል።

እራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል - ከጥቃቅን ብሔርተኛነታችን አልፈን እንድንሄድ በሚያስችለን የጋራ አፍሪካዊ አርበኛነት ስሜት ካልተነሳሳች አፍሪካ ህዳሴዋ ላይ ልትደርስ ትችላለች? ለግል ጥቅማቸው ብለው የአፍሪካን ህዝብ የሚያድኑትን ልናሸንፍ እንችላለን? በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ሰብአዊነት የገፈፈውን ድህነትስ ልናስወግድ እንችላለን? እንደ ሰብአውያን የሚገባንን ክብር ለማግኘትስ እንችላለን?

የዚህ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት የተከበሩ ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ በአንድ ወቅት እንደጻፉት፥ "ለዴሞክራሲ እና ለልማት ያለን ተስፋ አጣዳፊ በሆኑ ማህበራዊ ችግሮቻችን ላይ ማህበረሰቡን የሚጠቅም ስራ የሚሰራ የተማረ ዜጋ በሌለበት በተግባር ሊተረጎም አይችልም" ብለው ነበር።

በርግጥም ዛሬ እዚህ የተሰበሰቡት ምሁር ዜጎች ተግባራት ውስጥ አንዱ ሊሆን የሚገባው ለማህበረሰቡ ጥቅም በሚሰራው ስራ ውስጥ የአፍሪካን ህዳሴ እውን ለማድረግ የሚካሄደውን ታሪካዊ ተግባር ማካተት ነው። የአፍሪካ ልሂቃንም ችሎታቸውን በመጠቀም አፍሪካ በአንድነት ለእድሳትዋ ለመስራት እንድትነሳሳ የሚያስችላትን ማእከላዊ የመሰባሰቢያ ሃሳብ እንድታገኝ ሊረዷት ይገባል።

የዘመናችን ምሁራንም የ19ኛው ክፍለ ዘመን ልሂቃኖቻችንን ፋና በመከተል አፍሪካ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ባለቤትነትን እንድታውጅ የሚያስችላት አዲስ ኢትዮጵያዊነት እንዲወለድ ሊሰሩ ይገባል።

---

## በወልቃይት ጠገዴ እና በተቀረው የአገሪቱ ክፍል የሚደርሰውን ግፍ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ አገዛዝ የአካባቢውን ነዋሪዎች የሚያሰቃይበትና ከምድር በታች የተገነባ እስር ቤት እንዳለው የሚገልጹት አቶ አባይ፤ በርካቶች በዚህ ቦታ ታጉረው ማለቃቸውን ገልጸዋል። ከዚህ ባሻገርም የወልቃይት ሴቶች ሆን ብለው በትግራውያን ወንዶች እንዲደፈሩ እንደሚደረግና፤ አንድ ወንድ በርካታ ሴቶችን እየደፈረ ልጅ ማስወለድ ማየት ባካባቢው እየተለመደ መምጣቱም ታውቋል።

አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በአካባቢው ስለሚደርሰው ግፍ የማይናገሩበትን ምክንያት የተጠየቁት አቶ አባይ፤ ጉዳዩን ለአለማቀፉ ማህበረሰብ ሊያደርስ የሚችል ከአካባቢው የወጣ የተማረ ሰው ሃይል እጥረት ከመኖሩ በተጨማሪ፤ ያለው የተወሰነ ጥረት እንኳ ፍሬ እንዳያፈራ የወያኔ አገዛዝ ከአካባቢው የሚወጣን መረጃ ከማፈን አኳያ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ ገልጸዋል።

አቶ አባይ መንግስቱ፣ በወልቃይትም ሆነ በተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚካሄደው ግፍ እንዲያበቃ ለዴሞክራሲ የቆሙ ድርጅቶች የፖለቲካ ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን በመተው ሊታገሉ ይገባል ሲሉ መክረዋል።

## ስብሃት ነጋ ከአንድ የቻይና ኩባንያ 150 ሚሊዮን ዶላር ጉቦ ተቀብሏል ተባለ

ከወያኔ ዋና ባለስልጣናት አንዱ የሆነው ስብሃት ነጋ ከአንድ የቻይና ኩባንያ በደላላነት ስም የመቶ ሃምሳ ሚሊዮን ዶላር ጉቦ ተቀብሏል ሲል አንድ አዲስ መጽሄፍ ወንጅሏል።

አዲስ ቮይስ የተባለው የመረጃ ድረ-ገጽ የገመገመው እና ዶ/ር አክሎግ ቢራራ በተባሉ የቀድሞ የአለም ባንክ ኢኮኖሚስት የተፃፈው መጽሃፍ፥ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ዚ.ቲ.ኢ ከተባለው የቻይና ኩባንያ ጋር 1.5 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ስምምነት በተፈራረመ ጊዜ፤ ስብሃት ነጋ የገንዘቡን አስር እጅ በደላላነት ክፍያ እንደተቀበለ ማጋለጡን ድረ-ገጹ ገልጿል።

የቻይና ኩባንያዎች በአፍሪካ ውስጥ የተለያዩ ትርፋማ ስምምነቶችን ለመፈጸም እንዲያስችሏቸው በሙስና የተዘፈቁ ባለስልጣናትን በጉቦ ማባበልን እንደ ልምድ እንደተያያዙት በሰፊው እንደሚነገርም ድረ-ገጹ ጠቅሷል።

ስብሃት ነጋ ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ከፍተኛ ሃብት ካጋበሱት ባልስልጣናት አንዱ ሲሆን፤ ከመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ጋር በገጠመው የውስጥ ለውስጥ ትግል ለጊዜው ተሸንፎ የወያኔ ኩባንያ ከሆነው ኤፈርት አመራርነቱ መወገዱ ይታወሳል።

## በዋሽንግተን ዲሲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በቻይና ኤምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ

በዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሐሙስ ሐምሌ 29 ቀን 2002 ዓም በቻይና ኤምባሲ ፊት ለፊት በመገኘት አገሪቱ ለዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የምታደርገውን ድጋፍ በመቃወም ሰልፍ አድርገዋል።

ሰልፈኞቹ፥ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ መረጃ እንዳያገኝ ለሚያደርገው እገዳ ቻይና የምትሰጠውን ድጋፍ እንድታቆም ጠይቀዋል። አገዛዙ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮን፣ የጀርመን ድምጽ ራድዮን፣ ኢሳት ቴሌቪዥንን እና የተለያዩ ድረ-ገጾችን ለማፈን የሚጠቀመውን ቴክኖሎጂ የሚያገኘው ከቻይና እንደሆነ በሰፊው ተዘግቧል።

የተቃውሞ ሰልፉ አዘጋጆች ቀደም ብለው ባወጡት መግለጫ፥ "ቻይና የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነት እና ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል በማገዝ ፈንታ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያላትን የኢኮኖሚ ጥቅም ብቻ ከግምት በማስገባት፤ የዜጎቻቸውን መብት እና የዴሞክራሲን ጥም ከሚያፍኑ አምባገነናዊ አገዛዞች ጎን እየቆመች ነው" ብለዋል።

ቻይና ለወያኔ አገዛዝ የምታደርገውን ቀጥተኛ ድጋፍ እንድታቆም ከመጠየቅ በተጨማሪ፤ በኢትዮጵያ በምታካሄዳቸው ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞችን መብት እንድታከብር፤ እንዲሁም የተለያዩ መንግስታዊ ኮንትራቶችን ያለ ጫረታ ለማግኘት ስትል ለወያኔ ባለስልጣናት ጉቦ መስጠትን እንድታቆም ሰልፈኞቹ ጠይቀዋል። ተቃውሞ ሰልፈኞቹ የቻይናን ባንዲራ ማቃጠላቸውንም ኢትዮሚዲያ የተባለው የመረጃ ድረ-ገጽ ዘግቧል።

## የንግድ ባለቤቶች ግብርን በተመለከተ ስሞታ እያሰሙ ነው

በአዲስ አበባ ከተማ የትናንሽ ንግድ ባለቤቶች ግብር በዝቶብናል በማለት ስሞታ እያሰሙ እንደሆነ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አሳይቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ተዘዋውሮ ያናገራቸው ግለሰቦች የተጫነባቸው መጠን ከአቅማቸው በላይ እንደሆነና መክፈል ተስኗቸው እስር ቤት እንሄዳለን ብለው እንደሚጠብቁ ገልጸዋል። ግለሰቦቹ፥ ለመጣጣር እና ልጆቻቸውን ለማዳን ሲሉ መንግስት ለጥቃቅን እና መለስተኛ ንግዶች የሚሰጠውን ብድር በመውሰድ ንግዶቻቸውን እንደጀመሩ የተናገሩ ሲሆን፤ ይህንን እዳቸውን በየወሩ ከነወለድ ከመክፈል በተጨማሪ የተጫነባቸው ግብር የማይቻል እንደሆነባቸው በምሬት አስረድተዋል።

ወያኔ በአሁኑ ሰዓት በስራ ላይ ያዋለው የግብር ስርአት ባብዛኛው በአድሎ የሚካሄድ የፖለቲካ መሳሪያ እንደሆነ ይታወቃል።

## የወያኔ እና የደጋፊዎቹ ኩባንያዎች በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር የሚያወጣ የመንግስት ኮንትራት ለብቻቸው ተቀራመቱ

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከ4.1 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ስድስት የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን ለአምስት ኩባንያዎች ሰጥቶ ስምምነት መፈራረሙን ሪፖርተር የተባለውና ከገዢው ፓርቲ ጋር ትስስር ያለው ጋዜጣ ዘግቧል።

ኩባንያዎቹም፥ መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ እንይ ኮንስትራክሽን፣ ኢትዮ-ጀነራል ኮንስትራክሽን እና ማክሮ ኮንስትራክሽን መሆናቸው ታውቋል። ሪፖርተር፥ መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ በመንግስት የልማት ድርጅትነት ስም ከአራት አመታት በፊት በወያኔ አገዛዝ የተመሰረተ መሆኑን ቢያሳውቀንም፣ ስለሌሎቹ ድርጅቶች ግን ያቀረበልን መረጃ የለም።

የዝግጅት ክፍላችን ባደረገው አጭር ምርመራ፣ ለጊዜው መረጃ ሊገኝበት ካልተቻለው ማክሮ ኮንስትራክሽን በስተቀር፣ የተቀሩት ድርጅቶች የወያኔ ወይም የደጋፊዎቹ ንብረቶች ናቸው። ሱር ኮንስትራክሽን የወያኔ ኩባንያ የኤፈርት ንብረት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ የኢትዮ-ጀነራል ኮንስትራክሽን ባለቤት ደግሞ አቶ ገብረህይወት አባዲ የተባለ እና ከአገዛዙ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው ግለሰብ ነው። ኢትዮ-ጀኔራል ኮንስትራክሽን የዛሬ አስር አመት የተመሰረተ ሲሆን፤ ያኔ የግንባታ እቃዎችን በመከራየት የጀመረው ኩባንያ አሁን ቢያንስ የ45 ሚሊዮን ብር ካፒታል ባለቤት እንደሆነ አዲስ ፎርቹን የተባለው ጋዜጣ ባለፈው አመት ዘግቧል።

በተደረገው ስምምነት የ428.7 ሚሊዮን ብር ኮንትራት የተሸለመው እንይ ኮንስትራክሽን ደግሞ የአቶ ይርጋ ሃይሌ ንብረት ነው። እንይ ኮንስትራክሽን ባለፈው አመት በአቅም ማነስ ምክንያት በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ተሰጥቶት የነበረን ኮንትራት የተቀማ እና በሌላ ጫረታ ውስጥ እንዳይገባ ተከልክሎ የነበረ ድርጅት ነው።

ይሁን እንጂ ባለፈው ሚያዝያ ወር ለወያኔ የምርጫ ቅስቀሳ ማካሄጃ በሚል ካገዛዙ ጋር ትስስር ያላቸው ነጋዴዎች ባካሄዱት የገንዘብ ማሰባሰቢያ፣ የእንይ ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ይርጋ ሃይሌ ለገዢው ፓርቲ 630 ሺህ ብር በመስጠት አንደኛውን ስፍራ እንደያዙ ካፒታል ጋዜጣ ዘግቦ ነበር። እንይ ኮንስትራክሽን በብቃት ማነስ ትናንሽ የከተማ ውስጥ ስራዎችን እንኳ ባግባቡ ለማከናወን አቅም የለውም እየተባለ የ428.7 ሚሊዮን ብር ኮንትራት መሸለሙም፤ አቶ ይርጋ የተለመደው ማስፈራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ ደጋፊነታቸውን ስላስመሰከሩ ሳይሆን እንደማይቀር አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔ ወይም የደጋፊዎቹ ንብረት ያልሆኑ የንግድ ድርጅቶች ከጊዜ ወደጊዜ በነፃነት ለመስራት እየተቸገሩ መሄዳቸው እና አብዛኞቹ የመንግስት ኮንትራቶች የሚሰጡት ለአገዛዙ ታማኝነታቸውን ላረጋገጡ እንደሆነ ይነገራል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ እንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org